ቁጥር OFAGF-04.16/1/22
ቀን 27/05/2012

ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክቡር አቶ በዛብህ ገብረየስ በየነ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ ፡ <u>የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 5 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 60 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች እና 3 ገጽ የሂሳብ ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

[illegible] ከበደ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥ ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኮሚሽኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>**

የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>**

1. በአጠቃላይ ብር 120,039.34 ኮሚሽኑ አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት አለአግባብ ክፍያ በመፈፀሙ የመንግስትን ውስን ሀብት አለአግባብ ወጪ እንዲሆን አድርጓል::

**<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>**

2. በድምሩ ብር 9,060,762.41 ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ ተረጋግጧል::

**<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>**

3. በአጠቃላይ ብር **569,316.60** የኦዲት ስራው እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ ተረጋግጦዋል::

ከላይ በተራ ቁጥር ከ1 እስከ 3 ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር በእኛ አስተያየት የኮሚሽኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ።

**<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣</u>**

ምንም እንኳን በሰጠነው አስተያየት ላይ ለውጥ ባያስከትሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- በድምሩ ብር 91,845,157.68 ሥራ ላይ አለመዋሉ ተረጋግጧል።

**<u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>**

- በርካታ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች በባለሙያ ሳይለዩ በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በአይነታቸው ሳይለዩ ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑ፣
- በርካታ መወገድ ያለባቸው ንብረቶች በቋሚ ዕቃ መጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፣
- የተለያዩ አዳዲስ የicmis ፕሮጀክት ንብረቶች እንዲሁም አላቂ ዕቃዎች (ብዛት 350 በክስ ፋይሎች፣ ቶነሮች) ወጪ ከተደረጉ በኋላ በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ከሚወገዱ ዕቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ በዕቃዎች ላይ ቢን ካርድ ከንብረቱ ጋር ያልተያያዘ (ለምሳሌ ብዛት 500 ናኖ እስክሪፕቶ፣ ብዛት ያለው ኦሞ፣ የሞተር ዘይት፣ ሶፍት) መሆኑ፣
- የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች በብዛት በቋሚ ግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኝ መሆኑ፣
- የንብረት ክፍሎች አካባቢ የአደጋ ጊዜ የእሳት ማጥፊያ የሌለው መሆኑ፣
- ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ተሽከርካሪዎች የተጠቀሙበት የነዳጅ መጠንና የሸፈኑት የኪሎ ሜትር ርቀት ማመዛዘኛ በዝርዝር የማይመዘገብ መሆኑ፣
- ከኮሚሽኑ ተሽከርካሪዎች መካከል ኢቲ 4-04259 እና ኢቲ 4-18428 የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፣

- ከኮሚሽኑ ተሽከርካሪዎች መካከል በመ/ቤቱ የባለቤትነት የስም ዝውውር ማድረግ ሲገባው ኢቲ 4-15362 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ኢቲ 4-14234 የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ስም መሆኑ፣
- ብዛታቸው 23 የሆኑ የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ነዳጅ በሌትር ስንት ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በሚመለከተው መ/ቤት ያልተገመቱ መሆናቸው፣
- የመንግሥት ተሿሚዎቹ ወደ ሌላ ተቋም ሲዘዋወሩ ለስራ ሲጠቀሙባቸው የቆዩት በስማቸው የተመዘገቡ ንብረቶችን እንዲመልሱ አለመደረጉን፣
- የኮሚሽን መ/ቤቱን መረጃ/ሠነድ ከሥጋት ነፃ የሚሆንበት የፀደቀ IT security policy የሌለ መሆኑ፣
- የኮሚሽን መ/ቤቱ መረጃ ከመ/ቤቱ ውጭ በሆነ መልኩ መጠባበቂያ (ባካፕ) ይዞ የማያስቀምጥ መሆኑ፣
- አይቲ ስትራቴጂክ ኮሚቴ ወይም እሱን የሚተካ የሌለው መሆኑ፣
- በክፍሉ ውስጥ የሚጠይቀው ሰራተኞች ብዛት 10 ቢሆንም፣ የሚገኙት 5 ብቻ በመሆኑ የዳታ ሴንተር ባለሙያ ባለመኖሩ ለክፍሉ ኃላፊነት የሚወስድ የሌለው መሆኑ፣
- የለሙ (የተጠናቀቁ) ሲስተሞች( ICSMIS, BSC Automation, LDMS, PORTAL and E-service) በተሟላ መልኩ ወደ ስራ ያልገቡ መሆኑ፣
- የመ/ቤቱ መረጃዎች በኮንትራት ሰራተኞች (በICSMIS ፕሮጀክት) ቁጥጥር ስር መሆኑ፣
- የICSMIS project የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በአግባቡ የዘረጋ መሆኑን ለማረጋጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
  - UPC-LCD Display የተሰበረ መሆኑ፣
  - UPS -2 ሙሉ ሲስተሙ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
  - Primary Cisco, manegment cisco ብዛት 2 እና Cisco IPS 4510 ብዛት 2 ዘመኑ የማይፈልጋቸው ስለሆነ ያለስራ በሰርቨር ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው፣

- አየር ፀባይ መቆጣጠሪያ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
- የሰርቨር ሩም የመኪና ማቆሚያ ውስጥ ክፍል ተሰርቶ ያለ ቢሆንም ከመኪና አደጋ ለመከላከል የሚስችል መከላከያ ያልተበጀለት መሆኑ፣

ተረጋግጧል።

- ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ወደ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ሲቀየር የመዋቅርና አደረጃጀት ለውጥ ጥናት በማድረግ የራሱን አወቃቀር በማጽደቅ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት ሳያስፈቅድ ከሐምሌ 01/2011 ጀምሮ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**